## ቴክሳስ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ የኢሕአፓ አባላት በኦስተን ከተማ ተሰበሰቡ
## በኢሕአፓ የተጠራም ሕዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ

ባለፈው አርብ ጥቅምት 27 ቀን (Nov. 6, 2009) ከቴክሳስ የተለያዩ ከተሞች የመጡ የኢሕአፓ አባላት አጠቃላይ ስብሰባ አድርገዋል። ስብሰባው የተካሄደው የቴክሳስ ዋና ከተማ በሆነችው ኦስተን ከተማ ሲሆን አባላት በአገራቸው እና በድርጅታቸው ዙሪያ አንገብጋቢ በሆኑ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይትን አድርገዋል። አገሪቱ የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ በስፋት የገመገሙ ሲሆን በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓትን እውን ለማድረግ እየተካሄደ ያለውን ሕዝባዊ ትግሉ ለማጎልበት የድርጅታቸው መጠናከር ወሳኝ መሆኑን አምነው ለዚህ ከፍተኛ መስዋዕትነት ለሚጠይቅ ተግባር ዝግጁነታቸውን በከፍተኛ የመነሳሳት ስሜት አስረግጠው ስብሰባቸውን ደምድመዋል።

እንዲሁም ቅዳሜ ጥቅምት 28, 2002 (Nov. 07-2009) በኦስተን የኢሕአፓ ኮሚቴ የተጠራና ከኦስተንና ከተለያዩ የቴክሳስ ከተሞች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት ሕዝባዊ ስብሰባ የተካሄደ ሲሆን የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል አቶ ፋሲካ በለጠ በእንግዳ ተናጋሪነት ተገኝተዋል። አቶ ፋሲካ በዚህ ስብሰባ ላይ ወቅታዊ በሆኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አድማጭን በሳበ አቀራረብ ትንታኔ ሰጥተዋል። አገራችን ከአምባገነን አገዛዝ ለማላቀቅ የታጋይ ኃይሎች ሚናና ተግባር ምን መሆን እንዳለበት አብራርተዋል። በስብሰባው ላይ ከተገኙት ኢትዮጵያውያን መካከል ከመቶ ስድሳ የሚሆኑት ወጣቶች ሲሆኑ ብዙዎቹ በኢሕአፓ ተሰባስቦ ለአገሩና ለወገኑ ለተዋደቀው ወጣት በሙሉ ያላቸውን አድናቆትና ከበሬታ ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ በሀገሪቱ ስላሉ የፖለቲካ፤የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች፤ ስለኢሕአፓ አላማና እንቅስቃሴ እንዲሁም በትግሉ ላይ በደረሰው አንዳንድ ችግሮች ምክንያት ሕዝቡ ከተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ተላቆ አስተማማኝ ወደሆነ ተሳትፎ ሊሸጋገር ስለሚችልበት ሁኔታ የተለያዩ ጥያቄዎች ተጠይቀው አጥጋቢ የሆኑ ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል።

በዕለቱ ስብሰባ በተሳታፊው በኩል ከፍተኛ የሆነ ለወገንና ለሃገር የመቆርቆር መንፈስ የታየበትና ውይይቱም ኢትዮጵያዊ ባህልና ከበሬታ በተሞላበት መንገድ የተካሄደ ነበር። ኢሕአፓ መሰል ስብሰባዎች እየጠራ ለአገር ወዳዱ ገለጻና ማብራሪያ መስጠት እንደሚገባው የሚያስገነዝቡና ትግሉን ለማጠናከር ፓርቲው በየጊዜው እርዳታና ትብብር ሊጠይቀን ይገባል የሚሉ ገንቢ አስተያየቶች ተደምጠዋል። ባጠቃላይ በስብሰባው ላይ የተገኙት ኢትዮጵያውያን ስለ አገራችን ጉዳይና ስለ ሕዝባዊ ትግሉ የሀሳብ አንድነትና የመንፈስ ውህደት የፈጠሩበት ስብሰባ ሲሆን ላካባቢው ኢትዮጵያዊያን ሁሉ አዎንታዊ ምሳሌ አድርገው በሚያነሱት መልክ ተጠናቋል።